በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር



# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 1-31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ

## ግምገማ እንዲሁም

## በፌብርዋሪ 2024

## የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 1/2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ - 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31 /2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረውየእርጥበት ሁኔታ - 4 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ - 6 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 7 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 7 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በጃንዋሪ በመጀመሪያው እና በሁለተኛዉ አስር ቀናቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ እንዲሁም በሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ከተጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም በበጋ ወቅት ዝናብ የማያገኙትን የሀገሪቱ አካባቢዎችን ጨምሮ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛውና በሰሜን ምስራቅ በአንዳንድ ቦታዎቻቸዉ ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበበት ወር ነበር፡፡

በአጠቃላይ በጃንዋሪ ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ የተስተዋለበት ቢሆንም፤ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እንዲሁም በአንዳንድ በመካከለኛውና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በአርባ ምንጭ 46.8 እና 22.7፣ በብላቴ 15.4 በጎሬ 28.3፣ በአማን 20.8 እና 17.1፣ በአንገርጉትን 15.3፣ በበደሌ 14.0፣ በቦሬ 12.0፣ በቡሬ 20.5፣ በቡርጂ 33.0፣ 14.6 በጭራ 45.2፣ 32.3 እና 45.2፣ በኮንሶ 23.6፣10.8 እና 12.0፣ በማጂ 11.5፣ በማሻ 10.6፣ 14.6 እና 12.6፣ በምዕራብ አባያ 12.0፣ በሳዉላ 27.2፣ በሻምቡ 15.2፣ ፣ በቁሉምሳ 11.0፣ በፓዌ 11.8፣ በቴፒ 15.9፣ በወላይታ ሶዶ 12.8፣ በአሊያ 36.4፣ በዶሎመና 10.0፣ በጋምቤላ 18.4፣ በጋቲራ 11.8፤ 17.4፣ በጂንካ 10.7፣ 33.3፣ 42.1፣ 15.5 እና 13.8፣ በሊሙገነት 11.5፣ በሚኤሶ 33.0፣ በአምባማሪያም11.4፣ በማጂ 35.5 እንዲሁም በተርጫ 36.8 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

በሌላ በኩል የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ 35-42 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል። ለአብነትም፡- በጋምቤላ 42 ዲግሪ ሴልሽየስ በ24 ሰዓት ውስጥ ተመዝግቧል፡፡




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፈው የጃንዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል የመዠንግና የአኝዋክ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ የጂማና የሰሜን ሸዋ ዞኖች እንዲሁም ከአማራ በጥቂት የምዕራብ ጎጃም ዞን ላይ ከ31-190 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ7-14 ቀናት ያህል የነበራቸው ሲሆን፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከጋምቤላ የኑዌር ዞን፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ የምዕራብ ጉጂና ጥቂት የቦረና ዞኖች፣ ኢሉባቦርና ቡኖበደሌ ዞኖች፤ ከአማራ የደቡብና ሰሜን ወሎ እናየደቡብ ጎንደር ምስራቃዊው ክፍል፤ ከአፋር ዞን 4 እንዲሁም የደቡብ ትግራይ ላይ ከ10-30 ሚ.ሜ ከ7 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ የጅማ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖበደሌ የምዕራብ ጉጂና ጥቂት የቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከአማራ የደቡብና ሰሜን ወሎ፣ የምስራቅ ጎጃም ዞን፤ የደቡብ ጎንደር ምስራቃዊው ክፍልና ሰሜን ሸዋ፤ ከአፋር ዞን 4፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ በጥቂት የመተከል ዞን እንዲሁም ደቡብ ትግራይ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31 /2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በጃንዋሪ ወር 2024 ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸው የተስተዋለ ሲሆን ይህም ሁኔታ ለድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበረ። በሌላ በኩል በመጀመሪያው እና በሁለተኛው አስር ቀናቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው የእርጥበት ስርጭት የነበራቸው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተለይም በወሩ መጨረሻ ቀናቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎችን ጨምሮ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛውና በሰሜን ምስራቅ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው የእርጥበት ስርጭት ያገኙ ሲሆን፤ ይህም የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረውየእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጃንዋሪ ወር በመካከለኛው እና በታችኛው አዋ ጊቤ፣ በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛውና የመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ በምስራቃዊ አባይ፣ በጥቂት የታችኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

የፌብርዋሪ ወር በመደበኛ ሁኔታ በበልግ አብቃይ አከባቢዎች የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የደቡብ ምዕራብ፣ የደቡብ፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በመጪው ፌብርዋሪ ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ እና ከመደበኛው በተሻለ ሁኔታ ለዝናብ መኖር ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በብዙ ስፍራዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንዲሁም በአንዳንድ አከባቢዎች ደግሞ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከፌበርዋሪ 1 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የፌብሪዋሪ ወር ከመደበኛው በተሻለ ሁኔታ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በልግ አብቃይ በሆኑ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ። ይህም ሁኔታ የበልግ ወቅት አምራች በሆኑት አካባቢዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ስለሚያሻሽል የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የተለያዩ የበልግ ወቅት ሰብሎችን አስቀድሞ ለመዝራት የሚያስችል በመሆኑ አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት አስፈላጊውን የዘር ግብዓት ከወዲሁ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚገኘው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠሩም በላይ ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል።

## ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የፌብሪዋሪ ወር የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ በዚህ መሰረት በላይኛውና በመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞ ጊቤ በላይኛው አዋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ እንዲሁም ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች የተሻለ እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን፤ ይህም የሚገኘው እርጥበት በተፋሰሶቹ ውስጥ ያለውን የውሃ ሀብት እንዲሻሻል አዎንታዊ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et